በኃጢአት፣ በውሸት፣ በፖለቲካ መሆን የለበትም። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም መድኃኒት ለመሆን በተወለደ ጊዜ በሄሮድስ ተንኮል ምክንያት ከእናቱ ጋር ሆኖ ወደ ግብፅ ተሰዶ ነበር ማቴ. 2፥13-18 በማስተማር ዘመኑም ችግር ሲገጥመው ከአንዱ ሀገር ወደ አንዱ ሀገር ይሄድ ነበር። ዮሐ. 4፥1-2 ለደቀመዛሙርቱ ሲያስተምር ባንዲቱ ከተማ መከራ ቢበዛባችሁ፣ ወደ ሌላይቱ ሽሹ ብሏል። ማቴ. 10፥23 በዚህም መሠረት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማስመሰል እንድንኖር ሳይሆን ስለ ጽድቅና ስለ እውነት ብለን መሰደድ እንደሚገባን በተግባርም በቃልም አስተምሮናል ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስም በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ ብሏል። 2ኛጢሞ. 3፥12 ሐዋርያት ወንጌልን የሰበከት እውነትነትን የተናገሩት በብዙ ስደት ነው። የመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን እስጢፋኖስ በተገደለ ጊዜ ታላቅ ስደት ገጥሟት ነበር። ሐዋ. 8፥10 ከዚህ በኋላ በዘመኑ በማዕታት ሁሉ ቤተክርስቲያን በስደት ነበረች። ስለዚህ ዛሬም ቢሆን በጽድቅ ምክንያት ስደት ቢገጥመን ብፁአን እንባላለን። ሀገርና ቦታ፣ ቤትና ንብረት ቢቀርብንም እግዚአብሔር ግን የማታልፈውን ሀገርና ቦታ ርስትና ቤት የሆነችውን መንግሥት ለማያትን ያወርሰናል። ጌታችን ስለዚህ ሲያስተምር ስለ ስሜ ቤቶችን ወይም ወንዶችን ወይም ሚስትን ወይንም ልጆችን ወይንም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል። የዘለዓለምን ሕይወት ይወርሳል ብሏል። ማቴ. 19፥29

ይህ አንቀጽ ስለ ጽድቅ መሰደድ መነቀፍንም በውሸት መታማትንና መጠላትንም ያጠቃልላል። ከዚህ ሌላ በስደታችሁ ሁሉ ደስታ እንዲኖረን ሐሴትን እንድናደርግ ያስተምራል። ሐሴት ማለት እጥፍ ድርብ ደስታ ማለት ነው። ደስ ሲለን የሚገባው ዋጋችን በሰማያት ታላቅ ስለሆነ ነው። የቀደሙ ነቢያትም እውነትን በመናገራቸው ምክንያት ተነቅፈዋል፣ ተጠልተዋል፣ ተሰደውማል። ዕብ. 11፥32-38 መድኃኒታችን በአሕዛብ ሁሉ ስለስሜ ስላስታማራችሁ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ ብሏል። ማቴ. 10፥22 ጌታና ሐዋርያትም በኋላ ሰማዕታትም እስከ ሞት የደረሱት በመነቀፍ፣ በመጠላትና በመሰደድ አስቀድመው ብዙ መከራ ካዩ በኋላ ነው። ዛሬ ግን ብዙዎች ደስ የሚላቸው ሲወደሱና ሲወደዱ ብቻ ነው። ነገር ግን በክርስቶስ ምክንያት ሲነቀፉ መከራ ሲደርስባቸው ደስ ሊላቸው ይገባል። በመከራችሁ ሁሉ ደስታዬ ከመጠን ይልቅ ይበዛል በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ተናግሯል። ስደት የሚሰጠውን ክብር ከዋጋ በላይ ስለሆነ ታላቅ ክብር ነው።

ስድስቱ ቃላተ ወንጌል

እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ለመኖር የሚያስችሉ የሰው ልጅ ወደ ሕይወት ጎዳና ለመራመድ መዘጋጀት ምክንያት የመሆኑ ስድስቱ ቃላት የተባሉ ሕግጋት ይገኛሉ። እነኝህም የሥነ ምግባር መሠረታዊ ሐሳች ናቸው። ክርስቶስም አጽንቶ ተናገራቸው። እነኝህን ሕግጋት በግልጽ ማወቅና መጠበቅ አለብን። ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘት ከፈለግህ ሕግጋትን መጠበቅ አስቡ ብሎናል ማቴ. 19፥16 የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ለሐዲስ ኪዳን ሕግጋት መሸጋገሪያ ሆነው አጥረው ተጠቃለው ከበድም ብለው ሐዲስ ኪዳን መታወቂያ መለያ ሕግ ናቸው።

እነዚህም፡ -

1. በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል።

2. ወደሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከርሷ ጋር አመንዝሯል
3. ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ አመንዝራ ያደርጋታል
4. ከቶ አትማሉ
5. ክፉውን በክፉ አትቃወሙ
6. ጠላቶቻችሁን ውደዱ

እስተውል እነዚህ ትዕዛዛት የብሉይ ኪዳን ፍፃሜ ናቸው፡፡ የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን ትዕዛዛት ጌታችን ከብሉይ ኪዳን ይልቅ የበለጠ በማጥበቅ አጥር በማበጀት አጽንቶአቸዋል፡፡ በሦስተኛው ደግሞ ማስተካከያ ሰጥቶበታል፡፡ በመጨረሻዎቹ ሦስት ትዕዛዛትን ግን የአራቱን ሽሮ በሐዲስ ኪዳን መንፈስ ለውጦአቸዋል፡፡

1. <u>አትግደል</u>፣ ሳለው ሕግ መፈጸሚያ አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል፡፡ እኔ ግን እላችኋለሁ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ የበደበውም ፍርድ ይባዋል፡፡ ማቴ. 5፣22 እኔ ግን እላችኋለሁ ሲል እውነተኛ አምላክነቱን በቀጥታ ያስረዳናል፡፡ እኔ ግን እላለሁ ኦሪትንስ ወንጌልንስ የሰራሁ አይደለሁምን? እኔ ግን ማለቱ ስለምንድን? ቢሉ "ጌታ ሁን፣ እንዳሻህ ሁን" ሳይሆን ይህስ በጌታ የለበትም ኦሪትን በሙሴ በኢያሱ አድሮ ሰርቶታል ወንጌልን ግን እርሱ ሰው ሆኖ ሰርቶታልና፡፡ አንድም ለቀደሙ ሰዎች እንዲህ ብዬ ነበር ዛሬ ግን እንዲህ እልኩ ማለቱ ነው፡፡ የቀደመውን ሕግ የሠራው እንዲህ መሆኑ አሁንም ከቶ አልሻረውም፣ አልናቀውም ግን ያንኑ አጠበቀው፡፡ ባለሥልጣንነቱን በመግለጽ ገለጸው እንጂ ለብሉይ አትግደል ስትል ለሐዲስ ግን ወንድምህን በከንቱ አታስቀጣ፣ አታሳዝን፣ አትስደብ ስል ለሞት ምክንያት የሚሆኑትን በሮች ዘጋ፡፡ ሥራውንም ቁረጠው፡፡ በብሉይ ወንድምህን ያለው እስራኤላውያንን ለእስራኤላውያን ነበር፡፡ ሐዲስ ግን የሰውን ነገድ የሆነው ሁሉ ነው፡፡ ሁሉም የአንድ የእግዚአብሔር ልጅ ነውና፡፡ በከንቱ የተቆጣ ማለቱ ምክንያት ካለ ይቆጣ ይጣላ ማለት አይደለም፡፡ ሕገ እግዚአብሔር ሲፈርስ ሕይወት ከመንፈሳዊ መስመር ውጭ ሆኖ ሲገኝ መምከር እምቢ ሲልም መቆጣት መገሰጽ ተገቢ መሆኑን ሲያስረዳ ነው፡፡ ወንድሙን ጨርቃም ብሎ የሚሰድብ በሸንጎ ይፈረድበታል፡፡ በማለት ለሞት ወይም ለመግደል ምክንያት ስለሆነ ነው፡፡ ቅጣቱን ከፍ አድርጎ የተናገረው ደንቆሮ በማለት የሚሳደብም ሰውየውን ብቻ ሳይሆን ፈጣሪውንም የሰደበ በመሆኑ በገሀነም እንዲፈረድበትና ቅጣቱን የበለጠ ከፍተኛ መሆኑን ገልጧል፡፡ እንግዲህ ነፍስ የገደለውማ ምን ያህል ከፍተኛ ቅጣት ያገኘው ይሆን፡፡ ከክርስቲያን አንደበት ሊወጣ ሊሰማ የሚገባው ምክር ተግሳጽ እንጂ ቁጣ ርግማን ስድብ ሊሆን አይገባም፡፡

2. <u>አታመንዝር ሳለው ሕግ መፈጸሚያ</u>፣ አታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል፡፡ እኔ ግን እላለሁ ወደ ሴት ያየ የተመኛትም በዚያን ጊዜ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል፡፡ ማቴ. 5፡ 28 ዘማዊ በመሆኑ ብቻ የሚፈረድበት አይደለም በሐሳቡ እንኳን የተመኘ ይፈረድበታል፡፡ ሰው በተግባር እንዳያመነዝር ብቻ ሳይሆን በልቡም ማመንዘር እንደሌለበት እንረዳለን፡፡ በዚህ መሠረት የልቡን ምንዝርና የሚያመጡትን ነገሮች ሁሉ ማስወገድ ይገባል፡፡ ሰው በዓይን በማየት፣ በመጥቀስ፣ በእጅ በመዳሰስና በመቆናጠጥ፣ በመተቃቀፍ በእግር በመጨፈርና

በመደነስ ሴት/ወንዱን/ ከተመኘ በልቡ አመንዝሯል። ይህ እንዳይሆን አሰናካይ የሆኑትን የዝሙት ዓይኖች የዝሙት እጆች እግሮች ማስወገድ ይገባል። የንጽሕናና የቅድስና አካላት እንድናደርጋቸው በነዚህ አማካኝነት የሚመጡ ሐሳቦችን እናጥፋቸው። ማለትን ያሳያል፤ ማቴ 5፣29

ወደ ሴት ያየ በልቡ አመንዝሯል ሲባል በምክንያት ወይም በአጋጣሚ በማኅበራዊ ኑሮና በባልንጀራነት ቀቃራኒ ጾታዎች ሳይተያዩ መኖር አለባቸው ማለት አይደለም። በእርግጥ ወንድ የሴት ስሜት ሴትም እንዲሁ ሊኖራቸው ይችላል። የተፈጥሮ ጠባይ ነውና። ይህ ዓይነቱ ስሜት እንደ ወንጀል ሊቆጠር አይችልም። ሰው ሁሉ ከባሕርይው ጋር የተያያዘ ነውና ነገር ግን አይቶ መመኘት ሆነ ብሎ የሠራው ጥፋት ይሁንብኝ ብሎ ያደረገው ስህተት ስለሆነ ያስጠይቃል። አይቶ፣ ሰምቶ ስሜትን ለልቡና ሳይሰጡ ያለፉት እንደሆነ ምንም አይደለም ≠ጢአትም አይደለም። ሰው የዝሙት ዋዜማ በሆነው በመዳራት ላይ የሚያሳያቸው ምልክቶች የልቡን ምንዝርና ይገልፁታል። ምናልባት በተግባር ያልፈጸመው የጊዜና የቦታ የሌሎች ሁኔታዎች አለመሟላት አግዶት ሊሆን ይችላል። ይህንንም ልብና ኩላሊትን የሚያይ ሕምላክ አጥርቶ ያውቀዋል። ኤር 17፣10 ንስሐ ካልገባን ≠ጢአት ሆኖ ይያዛል። ስለዚህ ክርስቲያኖች መድ≠ኒታችን ከዚህ እንድንለይ እንዳዘዘን አውቀን የልብ ምንዝርናን እናስወግድ።

<u>3. መፋታት ተገቢ አለመሆኑን የሚገልጥ ሕግ</u>

እኔ ግን አላችኋለው ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ የፈታችውንም ያገባ አመንዝሯል። ማቴ 5፣32

ሚስቱን፤ያለዝሙት ምክንያት የፈታ እንድትሰስን ከሕግ ውጪ እንድትሆን ምክንያት የሆነ እርሱ ስለሆነ በደሉ ወደ ወንድ እንደሚተላለፍ ተናገረ። እንዲሁም የተፈታችውን ያገባ አሁንም አመነዘረ። ባሏ እያለ ወደ ሌላ ወንድ የሄደች ሴት ባሏን እንደገደለች በሕይወትም እንደሌለ ስላደረገችው መፈታት አለባት እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን በራሳቸው ፈቃድ ሊለያዩ አይችሉምና። ጋብቻ ባሕርያዊ መሥጢራዊ እንደመሆኑ መጠን እግዚአብሔር የመሠረተው ነው። ያለበቂ ምክንያት በቃል ኪዳኑ ጋብቻን የመሠረቱ ባልና ሚስት መፋታት አይችሉም። ሙሴ የፍቺ ጽሕፈት በመስጠት ሰዎች በሆነው ምክንያት ፈቅዶ ነበር። ዘዳ 24፣1 ሙሴ ይህን ያደረገው ስለሰዎች ልብ ጥንካሬ እንደሆነ ጌታችን ለጠየቁት መልሷል። ማቴ. 19፣7 የክርስቲያን ጋብቻ በጌታ ቅዱስ ደምና ሥጋ የታተመ በመሆኑ እስከ ሞት ድረስ በታማኝነት በቃል ኪዳን መጽናት ይገባል። እንግዲህ በዝሙት ምክንያት ይህን የተቀደሰ ጋብቻ ያሰናከለ የክርስቶስና የቤተክርስቲያንን ሕብረት የካደ እና ቃል ኪዳን የረገጠ ሰው ስለሆነ በደሉ ከፍ ያለ ነው። ይህም የታተመው በሥጋወደሙ ነውና ጋብቻን ብናፈርስ ብናበላሽ ከኑሮ ጓደኛችን ብቻ ሳይሆን ከክርስቶስ ጋር ያለን ሕብረትና አንድነት ይፈርሳል። ስለዚህ ክርስቲያን በጌታ ደም በተገኘው ፍቅር ጋብቻቸውን እስከ ሞት ጠብቀው ሊይዙ ይገባቸዋል።

<u>4. መሐላን በሚመለከት፣ እኔ ግን እላችኋለው ከቶ አትማሉ ማቴ 5፣34</u>

ሰማይ ከነግሡ ምድር ከነልብሱ ራሳችንን ጨምሮ ሁሉም ነገር የእግዚአብሔር ነው። እንጂ እኛ በአንድም ላይ ማዘዝ አንችልም። ስለሆነም በምንም ነገር ጠቅሰን መማል እንደማንችል ይህ

ትዕዛዝ ያስረዳል። መሐላ ማለት አንድን ነገር ምስክር አድርጎ መጥራት ነው። በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን አንዳንድ ቅዱሳን በእውነት ለመመስከር ሲሉ የእግዚአብሔርን ስም በመሐላ ጠርተዋል። ዘፍ 21፥23 1ኛ ነገ 18፣ ገላ 1፥20 ቅዱስ ጳውሎስ &ሰዎች ከነሱ ከእነርሱ በሚበልጠው ይምላሉና ለማስረዳትም የሆነው መሐላ የሙግት ሁሉ ፍጻሜ ይሆናል& ይላል። ዕብ 63 16-18 ስለዚህ እውነት የሆነውን ቃል ለማስረዳት ያላቸው የመጨረሻ አማራጭ እግዚአብሔር ምስክርና ተጠሪ /ዋስ/ ለማድረግ ስሙን በመሐላ ቢጠሩ ≠ጢአት አይሆንም።

ነገር ግን በሐሰትና በሆነው ባልሆነው አስፈላጊ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ሥም በከንቱ እያነሱ መማል ≠ጢአት ነው። ነገሩ እውነት እንኳ ቢሆን ተሚጋች ከሌለውና ካላስፈለገ አዎን አዎ ወይም አይደለም ማለቱ በቂ እንደሆነ ጌታችን መድ≠ኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስረድቷል። ማቴ 5፥37 ቅዱስ ያዕቆብም በመልዕክቱ ጽፎታል። ያዕ 5፣ 37 ያዕ 5፥12 ከቶ አትማሉ ሲል በማያስፈልግና ከቶ አትማሉ ማለት መሆኑን ከዚህ እንረዳለን።

## 5. በአጠቃላይ የሕግ አፈፃፀም

እኔ ግን እላለሁ ክፉን በክፉ አትቃወሙ ለሚለምን ስጥ ከአንተም ይበደር ዘንድ ከሚወደው ፊቀቅ አትበል። በዚህ አንቀጽ ማንኛውም ነገር በትእግሥት እንድናሳልፈው ያስረዳል። ክፋት የዲያቢሎስ ነውና የዲያቢሎስ መገለጫ የመጣውን በሥነ ምግባር ማሸነፍ ነው። ዲያቢሎስ /ሰይጣንን/ ግን እንድንቃወመው ታዘናል። ያዕ 4፥7 ስለዚህ ክፉውን አትቃወሙ ሲባል ሰውን አትቃወሙ ማለት ነው። ክፉ ሰውን መለሰ መቃወም በክፋቱ መተባበር ነው። ሰውየውን ክፉ ያደረገውን ሰይጣን ነውና እኛንም ክፉ ለማድረግ ሰይጣን በሰዎች ይፈትነናል። ለሰዎች በክፋት ከመለሰን በሃሳብ ስለተፈጸመ ሰይጣንን አልተቃወምነውም ማለት ነው። ስለሆነም ጌታችን የቱሩፋትን ሕግ በማስተማር ለክፉ ሰው የበለጠ መልካም ነገርን እንድናደርግ አስተምሮናል። ቅዱስ ጳውሎስም በሮሜ 21፥21 ላይ «ክፉውን በመልካም አሸንፉ እንጂ በክፉ አትሸነፉ» ብሏል። ይህንን ትዕዛዝ የምንፈጽመው ብልሆች ሳለን በፈቃዳችን ራሳችንን በማሞኘት ነው። ክፉውን ለመቃወም አቅም ቢኖረንም በፈቃዳችን ደካሞች ሆነን ነው የክርስቲያናዊ ሕይወት መለኪያ የሥነ ምግባር ተገዥነታችንን የሚያረጋግጠው ይህ ትዕዛዝ ነው። ጌታችንና መድ≠ኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ራሱ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም። ሲቃወሙት አልተቃወመም ማቴ. 27፥12-14 1ኛ ጴጥ 2፥ 23 ስለዚህ ክርስቲያን በዓለም ላይ ክፉዎቹን ከሚቃወማቸው ይልቅ ሲጸልይላቸው ይገባል።

## 6. ፍቅር እንዴት እንደሚገለጥ ያሳያል

እኔ ግን እላችኋለሁ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የእግዚአብሔር ልጆች ትሆኑ ዘንድ። የሚረግሟችሁን መርቁ ስለሚጠሏችሁ መልካም አድርጉ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና። በጻድቃንና በ≠ጥአን ላይ ዝናምን ያዘንባልና። ማቴ 4፥44 በብሉይ ኪዳን ጠላትህን ጥላ ወዳጅህን ወደድ የሚል ሕግ ነበር። ጌታችን ግን ይህንን በዚህ ጠላቶቻችሁን ውደዱ በሚለው ሕግ ይሽረዋልና። ለበማዩ አባታችን እንሆን ዘንድ ጠላቶቻችንን ልንወድ ይገባል። እግዚአብሔር የወደደን፣ ያፈቀረን፣ በልጁ ሞት የታረቀንም ገና ከ≠ጢአታችንና ጠላቶቹ ሳለን

ነበር ። ሮሜ 5፣8-10 ቆላ 1፣2-22 ስለዚህ ልጆች ለመሆን ከፈለግን እርስ በርሳችን ልክ እንደ እንደወደደን መዋደድ አለብን። ፍቅራችን የማያዳላ መሆን አለበት። ነገር ግን የሚወደንን የምንወድ ከሆነ የሚጠላንን የምንጠላ ከሆነ ከአይሁድና ከአሕዛብ በምን እንለያለን? ይህ ጠላትን ጭምር ሰውን ሁሉ መውደድ የክርስቲያኖች ልዩ ምልክት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ጠላትህ ቢራብ አብላው ቢጠማ አጠጣው ይላል ። ሮሜ 12፣ 20 ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚለው ትዕዛዝ የረገሟችሁን መርቁ ለሚጠሉአችሁ መልካም አድርጉ ስለሚያሳድዷችሁ ጸልዩ በማለት አብራርቷል። ሮሜ 12፣14 በአጠቃላይ በፍቅሩ ምክንያትና መነሻ ስለማይኖረው የክርስቲያን እውነተኛ ፍቅሩ የሚታወቀው ጠላትን በመውደድ ነው። ክርስቲያናዊ ሕግ ፍፁምና ጠባብ በር ናትና። ማንም ሰው ጠላት ሊኖረው አይችልም የክርስቶስ ልጅ ነውና ቂም በቀልም አያስፈልግም አባታችን እግዚአብሔር ሐዳጌ በቀል ነውና ሁሉን ይቀር የሚል ነውና። ስድስቱ ቃላተ ወንጌል በአሥሩ ቃላት አንፃር የሚውሉ እነዚህ እንደሆኑ ቢነገርም በሌላ በኩል ደግሞ ስድስቱ ቃላት እየተባሉ የሚጠሩ ሌሎች እንደሆኑ ጌታ ለሁለተኛ ጊዜ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ ሰዎችን የሚጠይቃቸው እነዚህን ነው። እነዚህም ለሰው ሁሉ ሊደረጉና ሊፈፀሙ የሚገባቸው መሆኑን ገልጿል። ሰው የሆነ ሁሉ ወዶና ፈቅዶ ያለዚያም ተገዶ ሊፈጽማቸው የሚገቡ ናቸው።

## ስድስቱ ቃለተ ወንጌል

1. ተርቤ ነበርኩኝ አባላችሁኝ
2. ተጠምቼ ነበር አጠጣችሁኝ
3. ስደተኛ ነበርኩኝ ተቀብላችሁኝ
4. ታርዤ ነበርኩ አለበሳችሁኝ
5. ታምሜ ጎበኛችሁኝ
6. ታስሬ ነበሬኩ ወደ እኔ መጣችሁ

### 1. ተርቤ ነበርኩኝ አባላችሁኝ

ለጊዜው ተርቦ ሳለ ራሱንና ችግሩን የሚያስታግስበት የሚያስወግድበት የሚቀምሰውን መስጠት ያመለክታል። የተቸገሩ ወገኖች በየቤተክርስቲያኑ በየመንደሩ በየአስፋልቱ በየጥጉ ወድቀው ይገኛሉና። ስመ እግዚአብሔርን በመጥራት ይማፀናሉና። በሌላ በኩል ደግሞ ምዕምናን የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት ተርበዋልና። ከቅድስት ቤተክርስቲያን ጡት ወተቷን የቀመሰ ሁሉ የተማረውን ማስተማር የእግዚአብሔርን ቃልን መመገብ እንዳለበት ያመለክታል። ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርምና በእግዚአብሔር ቃል እንጂ ማቴ 4፣3 ዘዳ 8፣3 እንዲሁም የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መቀበል ፈልጎ ተርቦ ይሆናል። በየጊዜው ቅዱስ ቁርባን ማቀበል የካህኑ ግዴታ እንዳለበት ያስረዳል። የረሀብ ዓይነት ብዙ ነውና። ቤተክርስቲያንም በሁሉ ምልዕ ናትና በሁሉ መልክ አብልታ ታረካናለች።

### 2. ተጠምቼ ነበር አጠጣችሁኝ

ቀዝቃዛ ውኃ ያጠጣ በችግሩ ጊዜ የረዳ ዋጋ አለው ማለቱ ነው። እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቃል ማጠጣት ሊሆን ይችላል። ዮሐ 7፣38 ስለዚህ ካህናት የምእመናንን ፍላጎት ማርካት ከሥጋው ማብላት ከደሙ ማጠጣት ግዴታቸው ይሆናል። የቤተክርስቲያን ልጅነት በሥጋም በነፍስም የተሟላ ሕይወትን አግኝቶ መኖር ነውና። የተጠማ ሰውነት በንፁህ ውሃ ደረቁን ሰውነት ማጠጣት ማለምለም ተገቢ ነውና። ሥጋ ያለውኃ ነፍስም ያለ ቃለ እግዚአብሔር አይኖርም።

## 3. ስደተኛ ነበርኩኝ ተቀበላችሁኝ

እንግዳ በሚችሉት አቅም ማስተናገድ ተቀብሎ ማሳደርን ያመለክታል። በቤተክርስቲያናችንም ዘወትር ይነገረናል። በሀገራችን ልማድ፣ ባሕል ቤት ለእንግዳ ቤት የእግዚአብሔር ነው እየተባለ ይነገራል። ጌታም በወንጌሉ ቀዝቃዛ ውሃ የሰጠ ዋጋው አይጠፋም። ብሏል ማቴ 10፥42። ስደተኛ ከላይ ጥላ ከታች ጫማ ከፊት ከኋላ እቅፍ ድግፍ የሚያደርጋቸው ዘመድ አዝማድ የላቸውም እና ለሀገር እንግዳ ለሰው ባዳ ናቸውና ስደተኛን መቀበል ለክርስቲያን ወጉና ክብሩ ነው።

## 4. ታርዤ ነበርኩ አለበሳችሁኝ

እግዚአብሔር አምላክ በፈቀደ ሁለት እጅ ጠባብ ያለው አንዱን ለሌለው እንዲሰጥ ያስተምረናል። ሰው ካልለበሰ ከእንስሳት ያንሳልና። ፀጋውም ክብሩም ይረክሳልና ለታረዘ ማልበስ ፀጋን መጎናፀፍ ነውና። አዳም በኀጢአቱ ከፀጋው ታረዘ እኛ በኀጢአታችን መታረዝ እንዳይኖርብን ክቅድስት ቤተክርስቲያን አባቶች የንስሀ ልብስ በወንጌል ተመርተን እንልበስ እናልብስ። ከቃሉ ያፈረዝን ብዙ ነገና ኔርቃናችንን እየተገዝን የሰው መሳቂያ ሆነናል። ሥነ ምግባርን ልብስ አድርገን መልበስ አለብን።

## 5. ታምሜ ጎበኛችሁኝ

ሰው የሆነ ሁሉ ለታመመ ወንድሙ በጎ አድራጎትን መፈጸም አለበት። ይህንን አመጣችሁልኝ ይህንንና ይሄንን ሰጣችሁኝ አላለም። ነገር ግን አቅሙ በፈቀደው ማጽናናት በሃሳብ በገንዘብ በሌሎችም እንድንጎበኛቸው በሽተኞችን እግዚአብሔር ይማርህ ማለት ምግባቸው ነውና። በየጸበሉ በየሆስፒታሉ በየቤቱ የአልጋ ቁራኛ የደዌ ዳኛ ሆነው መጻጉእን የመሰሉ አሉና። መጠየቅ የእግዚአብሔር የምህረት እጅ እንድትቀርብ መጸለይ ለክርስቲያን የዕለት ተዕለት ተግባር ነውና። በሌላም በኩል ቃሉን አጥተው በነፍስ ታመው ይሆናል። ቃለ ሕይወት ወንጌልን ለታመመው ነፍስ መስጠትና በቃሉ ማዕድነት መጠየቅ ተገቢ ነው።

## 6 ታስሬ ነበርኩ ወደ እኔ መጣችሁ

የታሰረን ሙነብኝነት ማነጋገር ችግሩን ጠይቆ ተረድቶ ለማቃለል መሞከር ትልቁ ክርስቲያናዊ ተግባር ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌ የታሰሩትን ያስፈታቸው ነበር። እኛም የታሰሩትንና ያለአግባብ በሐሰት የተፈረደባቸውን በየእስርቤቱ የሚማቅቁትን ወገኖች መጠየቅ ይገባናል። በየእስር ቤቱ የሚሰቃዩ አሉና። እግዚአብሔር ያስፈታህ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። በነፍሳችንም የታሰርን ብዙ ነንና በሃጢአት ገመድነት በንሰሐ የፊጥኝ የታሰርን አለንና በቃሉ አስፈችነት ልንጠያየቅ ይገባል። የበረታው የደከመውን በመጠየቅ ከሃጢአት እስር ልንፈታ እንችላለን።

እነዚህን ስድስት ትዕዛዛት ያከበሩትን በሥራም የገለጡትን ክርስቲያኖች እውነተኛ ፈራጅ ጌታችን መድሃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ በክብሩ ሲቀበላቸው በጉባዔም ሲያስመሰግናቸው ደግነት ልማዳቸው የሆነ በሥነ ምግባር ያጌጡ ክርስቲያኖች መቼ ይኸን ሠራንልህ መቼስ ይሄን አደረግንልህ እያሉ እንደሚመልሱለት ከትሩፋት ወደ ትሩፋት መሄድ ልማዳቸው ነውና

በትሕትና ቃል ሲጠይቁት ያሳያል፡፡ ሰማያዊ ንጉሥ ክርስቶስ ግን ይኸን ሁሉ ለወንድሞቼ ለችግረኞቹ ያደረጋችሁት ስለኔ ስለኔ ለእኔ እንዳደረጋችሁት እቆጥርላችኋለሁ ሲል ተናግሯል፡፡ ማቴ 25፣31-40

## የጽድቅ ሥራ

**ጽድቅ ማለት፣**

- ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ስሜት ማግኘት ወይም መኖር ማለት ነው፡፡ የሥነ ምግባርን ሕግ ሁሉ ለመፈጸም ንፁሕና ፍፁም የሆነ ፍቅር እግዚአብሔር ያለው ሆኖ መገኘት ከፍቅሩ የተነሣ ፍቃዱን ለመፈጸም የሚያደርገው ጥረት፡፡
- በሰይጣን ላይ መሰልጠን /ድል መንሳት/፣ የእግዚአበሔርን መንግሥት ለመውረስ ብቁ ሆኖ መገኘት፣ በእውነት ጎዳና መራመድ ምግባረ ሰናይ መፈጸም፡፡
- በእግዚአብሔር ምሥጋና ጸንቶ መኖር ወዘተ የጽድቅን ቦታ ለመያዝ የጽድቅን ግብር የሆኑትን ሁሉ ለመፈጸም በግድ ያስፈልጋል፡፡
- ባመኑት እምነት ጸንቶ መኖር፡፡
- የጽድቅን ሥራ ለመሥራት በጎ ፈቃድ ያለው ሆኖ መገኘት
- የሚሠራውን የሚያምን፣ የሚያምነውን የሚሠራ ሆኖ መገኘት፡፡ ለጽድቅ የሚያበቃውን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ተግቶ በመሥራት ጽድቅ ይገኛል፡፡ ያዕ 2፣21-24 ሮሜ 2፣13

በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉም፡፡ ሮሜ 2፣13& ከአምላክና ከባልንጀራ ፍቅር የተነሳ መፈጸም አለበት፡፡ ማቴ 22፣37 የጽድቅ ሥራ በሁለት ከፍለን መመልከት እንችላለን፡፡

### እግዚአብሔርን የሚመለከቱ ሥነ ምግባሮች የጽድቅ ሥራዎች

ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚውሉ እግዚአብሔር ህልዎት አምለኮት መግለጫ የሚሆኑ የጽድቅ ሥራዎች ናቸው፡፡ ስለ እርሱ በቀጥታ የሚናገሩ፣ የሚሠሩ ለሱ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ/ እግዚአብሔርን መፍራት | ለ/ ሃይማኖት | ሐ/ ተስፋ | መ/ ፍቅር |
| ሠ/ ቅድስና | ረ/ ጸሎት | ሰ/ ጾም | ሸ/ ምፅዋት |
| ቀ/ ጽድቅ | በ/ ንጽሕና | | |

### ሰዎችን የሚመለከቱ የጽድቅ ሥራዎች

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ/ ጥበብ | ለ/ አስተዋይ | ሐ/ እውነተኛ | መ/ ታማኝ |
| ሠ/ ንቁ ... ረ/ ጽኑእ | | ሰ/ ትዕግስተኛ | ሸ/ ጨዋነት |
| ቀ/ ትህትና | በ/ ሰላማዊነት | ተ/ ልበ ሰፊ | ቸ/ ህጻጌ በቀል |
| ነ/ ገር/ደግ/ | ኘ/ ለጋስ | አ/ ደስተኛ | ከ/ አማኝ ወዘተ |

## የሐጢአት ሥራ

ለእግዚአብሔር ሕግ በፈቃድ አለመገዛት በሃሳብም በንግግርም በሥራም ይህንን በመሳሰሉት ሁሉ አለመታዘዝን መግለጽ ነው፡፡